# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# መልካም ነገስታት
# ፦ክፉ ነገስታት

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Lazarus, Alastair Paterson

ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ለምናሴ እጅግ የማያስደስት ቀን ነበረ፡፡ አባቱ ፣ ንጉስ ሕዝቅያስ ሞቷል፡፡ አሁን ፣ የአስራ ሁለት አመቱ ምናሴ በይሁዳ ላለው ሕዝብ አዲሱ ንጉስ ሆኗል፡፡ ያንን በፊት አላወቀውም ነበረ ፤ ነገር ግን ምናሴ ለሃምሳ አምስት አመታት ንጉስ ሊሆን ነው፡፡ መልካም ንጉስ ለመሆንም ምናሴ የእግዚአብሔርን እርዳታ ፈልጓል፡፡



ነገር ግን ምናሴ እግዚአብሔርን አስወግዶ ፣ ክፉ መሪ ሆነ፡፡ ለጣኦት አምልኮም መሰዊያን ሰራ፡፡ የተቀረጸን ምስል ሰራና ፣ በእግዚአብሔር መቅደስም አኖረው፡፡ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል እንዲህ ብሎ ነበረ ፣”የተቀረጸውን ምስል ለእኔ አታድርገው ፤ እንዳትሰግድላቸው ፣ እንዳታገለግላቸውም፡፡”



ምናሴ ጥንቆላንና አስማትን
ይለማመድ ነበረ፡፡ ሰዎችንም
ከእግዚአብሔር ውጪ ይመራ ነበረ፡፡
ልጁንም መስዋእት አድርጎ ለጣኦታት
ያቀርብ ነበረ፡፡ የምናሴ አለመታዘዝ
እግዚአብሔርን አሳዘነው፡፡



ሕዝቡ ሳይታዘዘው ሲቀር ፣ እግዚአብሔር እንዲቀጡ ይላቸው ነበረ፡፡ ይሔም በምናሴና እርሱ በሚመራቸው ሕዝብ ይሆን ነበረ፡፡ እግዚአብሔር የአሶራዊያንን ሰራዊት በእነርሱ ላይ ያመጣ ነበረ፡፡ ምናሴም በሰንሰለት ታስሮ ወደ ባቢሎን ተወሰደ፡፡



በባቢሎን በስቃይ እያለ ፣ ምናሴ እግዚአብሔርን ተማጸነ፡፡ በአባቶቹ አምላክ ፊት ራሱን አዋርዶ ፣ ጸለየ፡፡ ከዚህ በኋላ ፣ ሕያዋን ላልሆኑ ጣኦታት መጸለይ የለም፡፡ ነገር ግን ፣ ከዚህ ሁሉ ክፉ ድርጊቱ በኋላ ሕያው አምላክ ለምናሴ ሊመልስለት ይችላል?



አዎ! እግዚአብሔር የንጉሱን ጸሎት ሰምቶ ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው ፤ ወደ ንግስናው ፤ በሕዝቡ ላይ ንጉስ ወደ ሚሆንበት፡፡”





ንጉስ ምናሴ አዲስ ሰው ሆኗል፡፡ ከእግዚአብሔር መቅደስ ምስሎችን አውጥቶ ፣ ሁሉንም እንግዳ አማልክት በአንድነት ሰበሰባቸው፡፡ ሁሉንም ወረወራቸው፡፡ የእግዚአብሔርን መሰዊያ አድሰና የምስጋናን ስጦታ አቀረበ፡፡ ሕዝቡንም የእስራኤልን አምላክ እንዲያገለግል አዘዘ፡፡

እንዴት ያለ ለውጥ ነው በምናሴ የሆነው!



ምናሴ ሲሞት ፣ አሞን የሚባለው ልጁ ወደ ጣኦት አምልኮው ተመለሰ። ነገር ግን እንደ ምናሴ ራሱን በእግዚአብሔር ፊት አላዋረደም። አማን ኃጢያቱን ባበዛ ቁጥር ፣ አገልጋዮቹ በገዛ ራሱ ቤት ገደሉት። ለሁለት አመት ብቻ ነገሰ።



ቀጣይ የመጣው ንጉስ ኢዮስያስ የስምንት
አመት ልጅ ነበረ፡፡ ለሰላሳ አመታት ነግሶ
በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነውን ነገር
አደረገ፡፡ ክፉ አማልክትንና ክፉ የሆነን
አምልኮ አጠፋ፡፡ በእርግጥ ፣ ኢዮስያስ
ሁሉንም ጣኦታት በመሬት ላይ ጣላቸው፡፡



መልካም የሆነው ንጉስ ኢዮስያስ የእግዚአብሔርን
መቅደስ አጽድቶ ጠገነው፡፡ ከተጣሉት መካከል ፣
በሙሴ የተሰጠው የእግዚአብሔር ሕግ አንዱ ነበረ፡፡





ንጉሡም የሕጉን ቃል ሲሰማ ፣ በሐዘን ሸማውን ቀደደው ፡፡ ኢዮስያስም የእርሱ የቀደሙ ዘሮች እንዴት ያሉ ጩካኞች እንደሆኑ አወቀ፡፡

ኤልዳድ የሚባልም ነብይ የእግዚአብሔርን መልዕክት ለኢዮስያስ ላከለት፡፡ “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፣ እነሆ ፣ እኔን ትተውኛልና በዚህ መጽሐፍ ያለውን እርግማን ሁሉ አመጣባቸዋለሁ፡፡” ነገር ግን ፣ ኢዮስያስ ትሑትና እግዚአብሔርን የሚያዘዝ ስለነበረ ፣ ከሞተ በኋላም ይሔ ነገር በእርሱ ሕይወት አልሆነም፡፡



እግዚአብሔርም ኢዮስያስን ሕዝቡን
ወደ እርሱ እንዲመልሳቸው አገዘው፡፡
አንድ ቀን ፣ በጦር ሜዳ ውስጥ
ሰራዊቱን ሲመራ ፣ ኢዮሲያስ በጠላት
ከፉኛ ጉዳት ደረሰበት፡፡ አገልጋዮቹም
በሰረገላ አድርገው እርሱ ወደ ሞተበት
ስፍራ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት፡፡
ሁሉም ሰው አለቀሰ ፣ ስለ መልካሙ
ንጉሳቸው ስለ ኢዮስያስም ተቀኙ፡፡





ከዚያም በኋላ ፣ መንግስቱ አለቀ፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን ፣ ንጉስ በእስራኤል ላይ ይነግሳል፡፡ ስሙ ፣ የነገስታት ንጉስ ፣ የጌቶች ጌታ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጣ ፣ የተጣለና የተሰቀለ ነበረ፡፡ እየሱስ ዳግም ሲመጣ ፣ በኢየሩሳሌም ላይ ብቻ አይደለም የሚነግሰው ፣ በአለም ሁሉ ላይ እንጂ፡፡

መልካም ነገስታት ፤ክፉ ነገስታት

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

2ኛ ዜና 33-36

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

23

60

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16